የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0013/15
ቀን/Date ሐምሌ 08 2014

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ:- <u>የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የወጪ ንግድ ምርት ናሙናዎች አቀባበል እና አላላክ መመሪያ ቁጥር 72/2014 ስለመላክ፤</u>

የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/890 ቀን 05/11/2014 በተጻፈ ደብዳቤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 32(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የወጪ ንግድ ምርት ናሙናዎች አላላክ እና አቀባበል መመሪያ ያዘጋጀ መሆኑን እና መመሪያው በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 16 መሠረት በፍትሕ ሚኒስቴር በኩል እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑን በመግለጽ መመሪያው በስራ ላይ እንዲውል የመመሪያውን ቅጅ ልከዋል።

በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በስራ ላይ እንዲውል የላከው "የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የወጪ ንግድ ምርት ናሙናዎች አቀባበል እና አላላክ መመሪያ ቁጥር 72/2014" በጥንቃቄ ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ የመመሪያውን ቅጅ 22 ገጽ በዚህ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለአምራችና ወጪ ንግድ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለኮሚኒኬሽን የስራ ሂደት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>


ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ፖ.ሳ.ቁ. 2559

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. ገ/ለ1/2/890

ቀን / Date 5/11/2014

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 32(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የወጪ ንግድ ምርት ናሙናዎች አላላክ እና አቀባበል መመሪያ አዘጋጅቷል።

መመሪያው በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ - ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 16 መሠረት በፍትሕ ሚኒስቴር በኩል እንዲመዘገብ ተደርጓል።

ስለዚህ መመሪያው በሥራ ላይ እንዲውል የመመሪያውን ቅጂ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
<u>አዲስ አበባ</u>

ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter/H/GT

ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 96 / 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲጽፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

# የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የወጪ ንግድ ምርት ናሙናዎች አቀባበል እና አላላክ መመሪያ ቁጥር 72/2014

ገንዘብ ሚኒስቴር
2014 ዓ.ም

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
በኢትዮጵያ ጉምሩክ
ቤት መዝገብትና
ቁጥር
No.
Ethiopian Customs C
Records & Docum

<u>መግቢያ</u>

በአለም አቀፍ ንግድ በአንድ አገር የተመረቱ ምርቶችን ናሙና ወደ ሌላ አገር እንደ ማሳያ፣ ማስታወቂያ እና ከገገር ደንበኞች ትዕዛዝ ለማግኘት መላክ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአገራችን እየሰፋ ከመጣው ኢንቨስትመንት ጋር ተያይዞ የምርት ናሙናዎች የመላክና የመቀበል ጥያቄ በዓይነትና በብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ፤

አምራች ላኪ ኢንዱስትሪዎች ከሚልኳቸውም ሆነ ከሚቀበሏቸው ናሙናዎች ብዛት እና ዓይነት ጋር ተያይዞ ግልፅ፣ ቀልጣፋ እና ተገማች የሆነ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የአገርን ዘላቂ ጥቅም ማስጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 32(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የወጪ ንግድ ምርት ናሙናዎች አቀባበል እና አላላክ መመሪያ ቁጥር 72/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. "ናሙና/sample/" ማለት የአንድ ምርት ወካይ ሞዴል ሲሆን አንድ ዓይነት ምርት በብዛት ከመመረቱ በፊት ምርቱን በጥራት፣ ስታይል (ዲዛይን) እና ሌሎች የምርቱ ባህሪያትን (characteristics) አንፃር ለመገምገም የሚያስችል ምርት ነው፡፡

2. **"የሴልስማን ናሙና/Salesman Sample/"** ማለት ከገገርው ኩባንያ በቀረበው የምርት ትዕዛዝ መሠረት ናሙናው ከተመረተ በኋላ በሽያጭ ማዕከሎች ውስጥ በቅድሚያ በማስተዋወቅ ደንበኞች እና ቸርቻሪ ደንበኞች በምርቱ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት እና በሚሰጡት አስተያየት መሠረት ማስተካከያ ለማድረግ የሚረዳ የናሙና ዓይነት ነው፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2
Ethiopian Customs Records & Documentation

3. **“ናሙና መላክ”** ማለት ናሙና ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ አምራች ላኪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ቢሮ ከፍተው በመስራት ላይ ወደሚገኙ ገገርዎች/ወኪሎች የመላክ ተግባር ነው፡፡

4. **“ናሙና መቀበል”** ማለት ናሙና ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ቢሮ ከፍተው በመስራት ላይ ከሚገኙ ገገርዎች/ወኪሎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደሚገኙ አምራች ላኪዎች የማስገባት ተግባር ነው፡፡

5. **“አምራች ላኪዎች”** ማለት በኢትዮጵያ የማምረቻ ፋብሪካ/ፋሲሊቲ ያላቸው በኢንዱስትሪ ፓርክና ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ የሚገኙ እና ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ አገር የሚልኩ ኩባንያዎች ናቸው፡፡

6. **“ገዥዎች”** ማለት በአለም አቀፍ ገበያ በአምራች ላኪ የተመረቱ ምርቶችን የሚገዙ ናቸው፡፡

7. **“ወኪሎች”** ማለት በአገራችን ቢሮ ከፍተው ገዥዎች ከአገራችን አምራች ላኪዎች የሚገዟቸውን ምርቶች በማምረትና በመላክ እንዲሁም የግዥ ትዕዛዝ ናሙናዎችን ከገዥው ወደ አምራች ላኪው በማድረስ ሂደት የሚያግዙ ኩባንያዎች (Buying houses or sourcing offices) ናቸው፡፡

8. **“ትሪምና አክሰሰሪዎች”** ማለት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ምርት ከተመረተ በኋላ ለማሸጊያ የሚያገለግሉ ምርቶች ናቸው፡፡

9. **“ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ”** ማለት ጥሬ ዕቃን በመጠቀም ጨርቃጨርቅ ግን፣ አልባሳትን፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶችን፣ ምግብና መጠጦች፣ መድኃኒቶችን፣ ኬሚካሎችን፣ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ እንዲሁም ኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስን ጨምሮ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን የማምረት፣ የመቀነባበር ወይም የማዘጋጀት ተግባራትን የሚያከናውን ተቋም ነው፡፡

10. **“ሚኒስቴር”** ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው

11. **የፆታ ስያሜ** በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ አምራች ላኪዎች በቀጥታ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በሚገኙ የገዥ ወኪሎች በኩል በሚልኳቸውና በቀጥታ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ባሉ የገዥ ወኪሎች በኩል ከውጪ በሚያስገቧቸው ናሙናዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ... ቤት መዛግብት ...
ቁጥር ...
No. ...
Ethiopian Customs ...
Records & Docum...

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

## ክፍል ሁለት

## የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምርት ናሙናዎችን ለመላክ እና ለመቀበል የሚያስፈልጉ መረጃዎች

4. **በአምራች ኢንዱስትሪው የሚቀርቡ መረጃዎች**

1/ የአልባሳት፣ የጨርቅ እና የክር ናሙና ምርቶችን ወደ ውጪ ለመላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚዘጋጀው ሰነድ በኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ መገለፅ ከሚገባቸው መሠረታዊ መረጃዎች በተጨማሪ

ሀ) የናሙናው ዓይነት፣
ለ) የገዥ ኩባንያ ስም፣
ሐ) ናሙናው ለሽያጭ አገልግሎት የማይውል ስለመሆኑ፣
መ) የእያንዳንዱ ናሙና ዋጋ እና
ሠ) የናሙና ምርቱ ዝርዝር መረጃዎች ማለትም የስታይል ቁጥር፣ የከለር፣ ልኬት (size)፣ የገዥ ትዕዛዝ ቁጥር እና ሌሎች አስፈላጊ መገለጫዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡

2/ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርት ጫማ፣ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች እና የጓንት ናሙና ምርቶችን ወደ ውጪ ለመላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚዘጋጀው ሰነድ በኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ መገለፅ ከሚገባቸው መሰረታዊ መረጃዎች በተጨማሪ

ሀ) የናሙናው ዓይነት፣
ለ) ናሙናው ለሽያጭ አገልግሎት የማይውል ስለመሆኑ፣
ሐ) የእያንዳንዱ ናሙና ዋጋ፣
መ) የምርት ናሙና ዝርዝር መረጃ (ስታይል ቁጥር፣ ከለር፣ ልኬት (size)) እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡

3/ የምግብ እና መጠጥ ናሙና ምርቶችን ወደ ውጪ ለመላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚዘጋጀው ሰነድ በኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ መገለፅ ከሚገባቸው መሰረታዊ መረጃዎች በተጨማሪ

ሀ) የናሙናው ዓይነት፣
ለ) የምርቱ ስም፣
ሐ) የአምራች ስም እና አድራሻ፣
መ) የተመረተበት ቀን፣

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

Ethiopian Customs Records & Docum

ሠ) ምርቱ የያዛቸው ንጥረ ነገሮች ዝርዝር (ይዘት) በአንድ ነጠላ ሁኔታ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡

ረ) የመጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን፣

ሰ) በኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን ለአምራች ላከው የፍቃድ ቁጥር፣

ሸ) ናሙናው ለሽያጭ አገልግሎት የማይውል ስለመሆኑ፣

ቀ) የእያንዳንዱ ናሙና ዋጋ እና

በ) የምርቱ ናሙና ዝርዝር መረጃ (የማኅር ትዕዛዝ መጠን (የማኅር ትዕዛዞች ከተሰጡ በኋላ ለሚኖሩ ናሙናዎች ብቻ)፣

ተ) የምርት ናሙናው መጠን ፣

ቸ) ዓይነት እና ሌሎች መግለጫዎችን ለያካትት ይገባል፡፡

4/ በኬሚካል እና የኮንስትራክሽን ዘርፍ የናሙና ምርቶችን ወደ ውጪ ለመላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚዘጋጀው ሰነድ በኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ መገለፅ ከሚገባቸው መሰረታዊ መረጃዎች በተጨማሪ

ሀ) የናሙናው ዓይነት፣

ለ) የገዥ ኩባንያ ስም፣

ሐ) ናሙናው ለሽያጭ አገልግሎት የማይውል ስለመሆኑ፣

መ) የእያንዳንዱ የናሙና ዋጋ እና

ሠ) የምርቱ ናሙና ዝርዝር መረጃ (የማኅር ትዕዛዝ ቁጥር (የማኅር ትዕዛዞች ከተሰጡ በኋላ ለሚኖሩ ናሙናዎች ብቻ)፣ የቀለም፣ የልኬት (size) እና ሌሎች መግለጫዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡

5/ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ እንዲሁም ኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ የምርት ናሙናዎች ወደ ውጪ ለመላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚዘጋጀው ሰነድ በኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ መገለፅ ከሚገባቸው መሰረታዊ መረጃዎች በተጨማሪ

ሀ) የናሙናው ዓይነት፣

ለ) የምርቱ ስም፣

ሐ) የአምራቹ ስም እና አድራሻ፣

መ) የተመረተበት ቀን፣

ሠ) ምርቱ የንጥረ ነገሮች ዝርዝር ምርቱ (ከአንድ በላይ ውህድ ካለው)፣ የአያያዝ ሁኔታ ያካተተ መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል፡፡

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
ሚኒስቴር



በኢትዮጵያ ጉ...
ቤተ መዛግብት
ቁጥ
No
Ethiopian Customs
Records & Docum

6/ የፋርማሲቲካልስ ዘርፍ ናሙና ምርቶችን ወደ ውጪ ለመላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚዘጋጀው ሰነድ በኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ መገለፅ ከሚገባቸው መሰረታዊ መረጃዎች በተጨማሪ

- ሀ) የናሙናው ዓይነት፣
- ለ) የምርት ስም፣
- ሐ) የአምራች ስም እና አድራሻ፣
- መ) የተመረተበት ቀን (የምርት ቀን)፣
- ሠ) የንጥረ ነገሮች ዝርዝር (ይዘት) - በአንድ ነጠላ ሁኔታ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል)፣
- ረ) የመጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን፣
- ሰ) አስመጪዎች የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን የፍቃድ ቁጥር፣
- ሸ) ናሙናው ለሽያጭ አገልግሎት የማይውል ስለመሆኑ፣
- ቀ) የእያንዳንዱ የናሙና ዋጋ እና
- በ) የናሙና ምርቱ ዝርዝር መረጃ (የግዥ ትዕዛዝ መጠን (የግዥ ትዕዛዞች ከተሰጡ በኋላ ለሚኖሩ ናሙናዎች ብቻ)፣
- ተ) የምርት መጠን ፣
- ቸ) ዓይነት እና ሌሎች መገለጫዎችን ለያካትት ይገባል፡፡

## ክፍል ሦስት

## በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ወደ ውጭ የሚላኩ እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የምርት ናሙናዎች መጠን

በአገራችን በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩ አምራች ላኪዎች ከዚህ በታች ከአንቀጽ 5 እስከ 9 በእያንዳንዱ ዘርፍ ሥር ለተጠቀሱት የምርት ዓይነቶች በተወሰነው መጠን መሠረት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው እና የባንክ ኤክስፖርት ፈቀድ ሳይጠየቅባቸው የምርቱን ናሙናዎች በቀጥታ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ቢሮ ከፍተው በሚሠሩ የገዥ ወኪሎች በኩል ወደ ውጪ መላክ ወይንም ከውጪ መቀበል ይችላሉ፡፡

### 5. የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ዘርፍ

#### 5.1 የአልባሳት (Apparal/Garment) ምርት ናሙና መጠን

ሀ) ከሲልስማን ናሙና ዓይነት ውጭ ያሉ ሁሉም የናሙና ዓይነቶችን ወደ ውጪ ለመላክ ለአንድ ገዢ ኩባንያ በአንድ ጊዜ ከአንድ ስታይል በአንድ የናሙና ዓይነት እስከ አስር (10) ናሙናዎችን፣ ነገር ግን በምርት ባህሪይ

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

በኢትዮጵያ ጉ...
ቤት መዝገብትና
ቁጥር
No
Ethiopian Customs
Records & Docum...

ምክንያት ከተጠቀሰው መጠን በላይ በናሙና መልክ መላክ አምራች ላኪዎች በሚከተለው አኳኋን መስተናገድ ይችላሉ፡-

1/ በናሙናዎቹ ላይ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ በናሙናው የውጭኛው ክፍል ላይ ከናሙናው ከለር ተቃራኒ በሆነ ከለር 2.5 ሴ.ሜ እና ከዚያ በላይ ከፍታ እንዲሁም 5 ሴ.ሚ እና ከዚያ በላይ ርዝመት ያለው "SAMPLE" የሚል ማህተም እንዲያርፍበት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2/ የናሙና ምርቱ የተመረተበት ጨርቅ ስስ እና ማህተሙን ለመቀበል አስቸጋሪ እና ምርቱ ላይ የሚያርፈው ማህተም ምርቱን የሚጎዳ በሚሆንባቸው ጊዜያቶች "SAMPLE" የሚል ማህተም ያረፈበት ሌላ ቁራጭ ጨርቅ በማዘጋጀት ከናሙና ምርቱ ጋር በቀላሉ መገንጠል በማይቻል መልኩ መጣበቅ/መያያዝ ይኖርበታል፡፡

3/ ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች በምርቶች ላይ ማህተም ማድረግ በማይቻልበት ሁኔታ ከናሙና ምርቱ ዋነኛው ክፍል እንዲሁም ልብሱ ሲለበስ በግልፅ ከሚታይበት ቦታ ላይ 2.5 ሴ.ሜ እና ከዚያ በላይ ዲያሜትር መጠን ያለው ቀዳዳ በክብ መቆረጥ ይኖርበታል፡፡

ለ) የሴልስማን የናሙና ዓይነት በባህሪው ከሌሎች ናሙና ዓይነቶች የሚለይና በአንድ ጊዜ ከ200-500 ብዛት ያላቸው ናሙናዎችን መላክ የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህን ናሙና ወደ ውጭ ለመላክ እንደማንኛውም ኤክስፖርት [illegible] ይኖርበታል፡፡ ይህውም እንደ መደበኛ ኤክስፖርት [illegible] ዲክላራሲዮን በመሙላት የባንክ የኤክስፖርት ፈቃድ ማግኘት [illegible] ለኤክስፖርት የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሐ) የካልሲ ምርቶች በማምረት ኤክስፖርት የሚያደርጉ አምራቾች የምርቱ ባህሪ የሚለይ በመሆኑ ለአንድ ገዥ ኩባንያ በአንድ ጊዜ፣ ከአንድ ስታይል፣ በአንድ የናሙና ዓይነት እስከ አስር (10) ጥንድ ካልሲ ናሙናዎችን፣

መ) የውስጥ ልብስ (under wear) በማምረት ኤክስፖርት የሚያደርጉ አምራቾች የምርቱ ባህሪ የሚለይ በመሆኑ ለአንድ ገዥ ኩባንያ በአንድ ጊዜ፣ በአንድ የናሙና ዓይነት፣ በአንድ ስታይል እስከ ስምንት (8) እሽግ (Pack) (አንድ እሽግ በቁጥር እስከ አስር (10) ምርቶችን ሊይዝ ይችላል) ናሙናዎችን፣

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

በኢትዮጵያ ጉ...
ቤት መዛግብትና
No
Ethiopian Customs
Records & Docu...

ሠ) የህፃናት ልብስ (kids wear) በማምረት ኤክስፖርት የሚያደርጉ አምራቾች የምርቱ ባህሪ የሚለይ በመሆኑ ለአንድ ገዥ ኩባንያ በአንድ ጊዜ፣ በአንድ የናሙና ዓይነት፣ በአንድ ስታይል፣ በአንድ ቀለም እስከ ሰባት (7) እሽግ (Pack) (አንድ እሽግ በቁጥር እስከ አስራ ሁለት (12) ምርቶችን ሊይዝ ይችላል) ናሙናዎችን፣

ረ) የአልባሳት ምርቶችን ለማምረት የትሪምና አክሰሰሪ ናሙናዎችን ከውጭ ማስገባት እንዲሁም በአገር ውስጥ የትሪምና አክሰሰሪ የሚያመርቱ አምራቾች ኤክስፖርት ለማድረግ ናሙና መላክ የሚያስፈልግ በመሆኑ ተመጣጣኝ የሆኑ የትሪምና አክሰሰሪ ናሙናዎችን ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ወይም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መላክ/መቀበል ይቻላል።

ሰ) በአገራችን ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚያመርቱ የጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች በአገራችን ቢሮ ከፍተው በመስራት ላይ ለሚገኙ ገዥ ኩባንያዎች ወይም ኤጀንቶች (Sourcing offices/Buying houses) የሚላከው የአልባሳት ናሙና ብዛት/መጠን ወደ ውጭ ለመላክ ወይም ከውጭ በሚገባው በተዘጋጀው አሰራር ሥርዓት መሠረት መስተናገድ ይኖርበታል።

ሸ) በአገራችን ቢሮ ከፍተው በመስራት ላይ የሚገኙ ገዥ ኩባንያዎች/ኤጀንቶች (Sourcing offices/Buying houses) ለሌሎች የአከባቢ አገራት ተወክለው የሚልኩና የሚላኩላቸውን ናሙናዎች በዚህ መመሪያ በተዘጋጀው አሰራር መሠረት ማስገባት ወይም መላክ ይችላሉ።

## 5.2 የጨርቅ (Fabric) ምርቶች ናሙና መጠን

ሀ) የጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች በናሙና መልክ ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የጨርቅ ምርቶች በአንድ ጊዜ፣ ለአንድ ገዥ ኩባንያ፣ በአንድ ስታይል፣ በአንድ ከለር እስከ 100 ሜትር ወይም እስከ 30 ኪሎ ግራም የሚመዝን ጨርቅ መላክ/መቀበል ይችላሉ።

ለ) የጨርቅ ቁራጭ (Fabric Swatches) ናሙናዎችን በሚልኩ/በሚቀበሉ የጨርቃጨርቅ አምራቾች ላይ ምንም ዓይነት ገደብ ሳይኖር መላክ ይችላሉ። ነገር ግን የቁራጮቹ መጠን በA4 እና A3 መጠን መሆን ይኖርበታል።

## 5.3 የክር (Yarn) ምርቶች ናሙና መጠን

የክር ናሙና ምርቶችን ወደ ውጭ አገር ለመላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት በአንድ ጊዜ፣ ለአንድ ገዥ ኩባንያ፣ በአንድ ስታይል፣ በአንድ ከለር እስከ 30 ኪሎ ግራም፣

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
በኢትዮጵያ ጉ...
ቤተ መዛግብትና...
Ethiopian Customs
Records & Docu...

## 6. የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ

### 6.1. የቆዳ ምርት ናሙናዎች መጠን

ጥሬ ቆዳና ሌጦ፣ ፒክል፣ ዌት ብሉ፣ ክረስት እና ያለቀለት ቆዳ በዘርፉ የተሰማሩ የቆዳ አምራቾች በናሙና ደረጃ ወደ ውጪ መላክ ወይም ማስገባት በአንድ ጊዜ እስከ 300 ካሬ ጫማ ወይም የፍየልና የበግ ሌጦ (skins) ከሆነ በቁጥር እስከ 60፣ የከብት ቆዳ (hides) ከሆነ በቁጥር እስከ 14 ወደ ውጭ መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባ ይችላሉ፡፡ የሌሎች እንስሳት ሌጦ ለመላክ/ለማስገባት ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች የተሰጠ ልዩ ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡

### 6.2. የጫማ ምርቶች ናሙና መጠን

ሀ) የጫማ አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለምና ቁጥር ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 12 ጥንድ የጫማ ምርት ናሙናዎች መላክ ይችላሉ፡፡

ለ) የጫማ አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለም፣ ቁጥር እና ዲዛይን (ስታይል) ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 20 ጥንድ የጫማ ምርት ናሙናዎች መላክ ይችላሉ፡፡

ሐ) የጫማ አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለም፣ ቁጥር እና ዲዛይን (ስታይል) ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 5 ጥንድ የጫማ ምርት ናሙናዎች ማስመጣት የሚችሉ ሲሆን የናሙናው ሶሉ ላይ የተቀደደ ወይም የተበሳ መሆን አለበት፡፡

መ) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ናሙናዎች ለሽያጭ ዓላማ የማይውሉ መሆኑን እና ናሙና ስለመሆናቸው የሚያስረዳ ኢንቮይስ በላኪው ድርጅት መዘጋጀት አለበት፡፡

ሠ) የጫማ አምራች ድርጅቶች ለአለም አቀፍ ኤግዚቢሽን በሚሄዱበት ወቅት በፋብሪካ ደረጃ እስከ 40 ጥንድ ጫማ ይዘው መውጣት እና ምርቶቹ በወጡበት ሁኔታ ተመላሽ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 6.3. የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ምርቶች ናሙና መጠን

1. የቆዳ ቦርሳ ምርቶች ናሙና

ሀ) የቦርሳ አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለምና መጠን (ትንሽ፣ መካከለኛና ትልቅ) ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 5 በቁጥር የቦርሳ የምርት ናሙናዎች መላክ ይችላሉ፡፡



የኢትዮጵያ ጉ... ቤት መዝገብትና ... No. Ethiopian Customs ... Records & Docum...
የገንዘብ ... የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

ለ) የቦርሳ አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለም፣ ዲዛይን (ስታይል) እና መጠን (ትንሽ፣ መካከለኛና ትልቅ) ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 7 በቁጥር መላክ እና እስከ 3 በቁጥር የቦርሳ ምርት ናሙናዎች ማስገባት ይችላል::

2. **የጓንት ምርቶች ናሙና መጠን**

ሀ) የጓንት አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለምና ቁጥር ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 6 ጥንድ የጓንት የምርት ናሙናዎች መላክ ይችላሉ::

ለ) የጓንት አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለም፣ ዲዛይን (ስታይል) እና ቁጥር ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 12 ጥንድ መላክና 6 ጥንድ የጓንት ምርት ናሙናዎች ማስገባት ይችላሉ::

3. **የቆዳ አልባሳት**

ሀ) የቆዳ አልባሳት አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለምና መጠን (ትንሽ፣ መካከለኛና ትልቅ) ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 3 በቁጥር የቆዳ አልባሳት የምርት ናሙናዎች መላክ ይችላሉ::

ለ) የቆዳ አልባሳት አምራች ላኪዎች የተለያዩ ቀለም፣ ዲዛይን (ስታይል) እና መጠን (ትንሽ፣ መካከለኛና ትልቅ) ያላቸው በአንድ ጊዜ እስከ 4 በቁጥር መላክ እና እስከ 3 በቁጥር የቆዳ አልባሳት ምርት ናሙናዎች ማስገባት ይችላሉ::

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2



በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
ቁጥር 2
No.2
Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation

## 7. የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ዘርፍ

ሠንጠረዥ 1. የምግብ ፣ መጠጥ እና የፋርማሲቲካል ምርቶች ናሙና መጠን

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) ገበያ የሚላክ ምርት ናሙና | | | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ብዛት በሞዴል | ሁኔታ | |
| 7.1 በምግብ ዘርፍ | | | | | |
| ሀ | እሴት ተጨምሮባቸው የታሸጉ ምግቦች | በኪ.ግ | ከ 2 እስከ 45 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | ስለማን ባለው የመንግስት አካል ወይም እዉቅና በተሰጠው አካል ደህንነቱ የተረጋገጠ መሆን አለበት |
| ለ | የስኳርና ጣፋጭ ምርት ውጤቶች | በኪ.ግ | ከ 2እስከ 45 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ሐ | ዘይት | በሊትር | ተቆልቶ የተፈተገ ሰሊጥና ሀልዋ | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| መ | ተቆልቶ የተፈተገ ሰሊጥና ሀልዋ | በኪ.ግ | ከ 1 እስከ 5 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ሠ | የተቆላ ሰሊጥ | በኪ.ግ | ከ 1 እስከ 5 | | |
| ረ | ማገና | በኪ.ግ | ከ 1 እስከ 5 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ሰ | ሌሎች የምግብ ምርቶች | በኪ.ግ | ከ 1 እስከ 45 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ሸ | የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች | በኪ.ግ | ከ 2 እስከ 45 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ቀ | ቅመማ ቅመምን | በኪ.ግ | ከ 2 እስከ 45 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| በ | ሌሎች የባልትና ዉጤቶች | በኪ.ግ | 2-5 ኪሎ ግራም | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| 7.2 የመጠጥ ዘርፍ | | | | | |
| ሀ | አነቃቂ መጠጦች | በሊትር | 700ሚሊትር እስከ 9ሊትር | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ለ | ቡና በጥሬ/የተቆላ | በእያንዳንዱ የምርት አይነት | 100 ግራም-250 ግራም | | |
| ሐ | ሻይ ቅጠል | በኪ.ግ | 750ግ-2 ኪ.ግ | | |
| መ | አልኮል ነፃ መጠጦች | በሊትር | 2- 12 ሊትር | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ሠ | አልኮል መጠጦች | በሊትር | 750ሚሊ. ሊትር እስከ 24 ሊትር | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ረ | ብቅል | በኪ.ግ | 2 ኪ.ግ እስከ 5ኪ.ግ | | |
| ሰ | ሌሎች ግብዓቶች | በሊትር | 1ሊ. እስከ 12 ሊ. | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| 7.3 የፋርማሲቲካል ዘርፍ | | | | | |
| | የኮስሞቲክስ ዉጤቶች | በቁጥር | 1 እስከ 12 ፒስ | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |


የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2



የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 2
No 2
Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation

## 8. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ዘርፍ

ሠንጠረዥ 2. የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ እንዲሁም ኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ ምርቶች ናሙና መጠን

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ምርት ናሙና | | | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ብዛት በሞዴል | ሁኔታ | |
| 8.1 | የኢንጂነሪንግ ምርቶች | | | | |
| ሀ | አውቶሞቢል፣ ባለሁለትና ባለሶስት ጎማ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ተሽከርካሪዎች | በቁጥር | 1 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ለ | ማሽነሪ | በቁጥር | 1 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ሐ | ኢኩፕመንት | በቁጥር | 1 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| መ | ሌሎች ኢንጂነሪንግ ምርቶች | በቁጥር | 1 | የሚመለስ (በጉምሩክ አሰራር መሰረት) | |
| ٤.2 | መሰረታዊ ብረታብረት ምርቶች | | | | |
| ሀ | ትቦላሬና የማዋቀሪያ ብረቶች | በቁጥር | 5 | ላይመለስ የሚችል | |
| ለ | ቆርቆሮ | በቁጥር | 5 | ላይመለስ የሚችል | |
| ሐ | አርማታ ብረት | በሜትር | 3 | ላይመለስ የሚችል | |
| መ | ሚስማርና ሽቦ | በኪሎ | 5 | ላይመለስ የሚችል | |
| ሠ | ሌሎች | በኪሎ | 3 | ላይመለስ የሚችል | |
| 8.3 | ኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ ምርቶች | | | | |
| ሀ | ሞባይል | በቁጥር | 1 | ላይመለስ የሚችል | |
| ለ | አምፖል | በቁጥር | 10 | ላይመለስ የሚችል | |
| ሐ | የመንገድ መብራት | በቁጥር | 2 | ላይመለስ የሚችል | |
| መ | ኬብል | በሜትር | 10 | ላይመለስ የሚችል | |
| ሠ | ዋየር | በሜትር | 15 | ላይመለስ የሚችል | |
| ረ | ሰርኪዩት ብሬከር | በቁጥር | 6 | ላይመለስ የሚችል | |
| ሰ | ቴሌቪዥን | በቁጥር | 1 | ላይመለስ የሚችል | |
| ሸ | የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ | በቁጥር | 6 | ላይመለስ የሚችል | |
| ቀ | ኢንቨርተር | በቁጥር | 2 | ላይመለስ የሚችል | |
| በ | ሶኬት | በቁጥር | 5 | ላይመለስ የሚችል | |
| ተ | ስዊች | በቁጥር | 5 | ላይመለስ የሚችል | |
| ቸ | ዩፒኤስ | በቁጥር | 1 | ላይመለስ የሚችል | |
| ኀ | የመብራት/የውሀ ቆጣሪ | በቁጥር | 3 | ላይመለስ የሚችል | ለሰርተፍኬሽን ከሆነ በቁጥር ከ20-30 ቆጣሪ ሊላክ ይችላል፡፡ ቆጣሪዎቹ የሚመለሱ ሲሆን በጉምሩክ አሰራር መሰረት በታክስ ተመላሽ ሥርዓት ይስተናገዳሉ |
| ነ | ሌሎች | በቁጥር | 1 | ላይመለስ የሚችል | |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2





በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር
No
Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation

## 9. የኬሚካል እና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ

### ሠንጠረዥ 3. የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ምርቶች ናሙና መጠን

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት ዓይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| 9.1. | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የመሠረታዊ ኬሚካሎች ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | Sulfuric acid(ሰልፈሪክ አሲድ) | ሊትር | 5 ሊትር | | ✓ | |
| ለ | Aluminum Sulfate(አልሙኒየም ሰልፌት) | ኪ.ግ | 10 ኪ.ግ | | ✓ | |
| ሐ | Hydrogen peroxide ( ሀይድሮጂን ፐር አክሳይደ) | ሊትር | 5 ሊትር | | ✓ | |
| መ | Ethiozinon 60%EC (ኢትዮዝኖን 60%EC) | ሊትር | 10 ሊትር | | ✓ | |
| ሠ | Ethiodemethrin 2.5 wdp (ኢትዮዲሜትሪን 2.5 wdp) | ሊትር | 10 ሊትር | | ✓ | |
| ረ | Ethiolathion 95%ULV (ኢትዮላቲዮን95%ULV) | ሊትር | 10 ሊትር | | ✓ | ›› |
| ሰ | Ethiopyrifos 24% ULV (ኢትዮ ፒሪፎስ24% ULV | ሊትር | 10 ሊትር | | ✓ | |
| ሸ | Sodium Lauryl Ether Sulfate (SLES) ሶዲየም ላውሪል ኢትር ሰልፌት) | ኪ..ግ | 15 ኪ..ግ | | ✓ | |
| ቀ | Sodiumsilcate(ሶዲየም ሲሊኬት) | ኪ..ግ | 15 ኪ..ግ | | ✓ | |
| በ | LABSA(ላብሳ) | ኪ..ግ | 15 ኪ..ግ | | ✓ | |
| ተ | Carbon dioxide (ካርበን ዳይ አክሳይድ) | ኪ..ግ | 1 ኪ..ግ | | ✓ | |
| ቸ | Concrete admixtures(grinding aid) | ኪ..ግ | 5000 ኪ..ግ | | ✓ | ለሲሚንቶፋብሪካ ግብዓት የሚሆን ሳምፕል ስለሆነ በመጠን ከፍተኛ ነው። ግራይንድንግ ኤይድ ሲሚንቶ ፋብሪካ ውስጥ ሲሚንት ሚል ክፍል ውስጥ የሚሰራ ናሙና ሲሆን ዝቀተኛው የሙከራ ጊዜ 24 ሰዓት ነው። |
| ኀ | Mortars (ሞርታር) | ኪ..ግ | 25 ኪ..ግ | | ✓ | |
| ነ | Refurbishment (ማደሻ) | ኪ..ግ | 20 ኪ..ግ | | ✓ | |
| ኘ | Waterproofing (ዋተር ፕሩፊንግ) | ኪ..ግ | 20 ኪ..ግ | | ✓ | |

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

Ethiopian Customs
Records & Docu

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት አይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| አ | Plasticizer(ፕላስቲሳይዘር) | ኪ.ግ | 20 ኪ.ግ | | ✓ | |
| ከ | super plasticizer(ሱፐር ፕላስቲሳይዘር) | ኪ.ግ | 20 ኪ.ግ | | ✓ | |
| ኸ | Retarder(ሬታርደር) | ኪ.ግ | 20 ኪ.ግ | | ✓ | |
| ወ | Accelerator(አክስሌሬተር) | ኪ.ግ | 20 ኪ.ግ | | ✓ | |
| ዐ | Bonding(ባይንዲንግ) | ኪ.ግ | 21 ኪ.ግ | | ✓ | |
| 9.2 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ ለቆዳ ማልፊያና ማለስለሻነት የሚያገለግሉ የኬሚካል ምርት ናሙናዎችመጠን | | | | | |
| ሀ | መሰረታዊ ኬሚካሎች (Basic chemicals) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው፣ |
| ለ | ሰው ሰራሽ አጋዥ የቆዳ ማልፊያ ኬሚካሎች (Syntans) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| ሐ | የቆዳ ማለስለሻ ዘይቶች (Fatliquors) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| መ | ዱቄትና ፈሳሽ ማቅለሚያ ኬሚካሎች (Powder and liquied dyestuffs) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| ሠ | የማቅለም ስራ አጋዦችና ማጠንከሪያዎች (Dyeing auxiliaries and fixatives) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| ረ | የላይ ወይም የቅብ ቀለሞች (pigments) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| ሰ | የማጠናቀቂያ ማጠናከሪያዎች (Binders) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| ሸ | የማጠናቀቅ ሥራ መደምደሚያዎች (Finishing lacquers) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| ቀ | የማጠናቀቂያ ቅባቶችና ዘይቶች (Wax emulsions and oils) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| በ | ኢንዛይሞች እና ሌሎች ኬሚካሎች (Enzymes and other chemicals) | ኪ.ግ | 5 ኪ.ግ | | ✓ | በ ታሪፍ ቁጥር……የሚመደቡ ግብዓቶች ናቸው |
| 9.3 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የሳሙና፣ ዲተርጀንት፣ ቀለምና ተዛማጅ ውጤቶች የምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | ደረቅ የልብስ ሳሙና (Laundry soap) | ግራም | 12,500-25,000 | | ✓ | |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
Ethiopian Customs
Records & Docum

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት አይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| ለ | ፈሳሽ ሳሙና (Liquid Detergent) | ሊትር | 10-30 | | ✓ | |
| ሐ | የዱቄት ሳሙና (Powder Detergent) | ግራም | 15,000-25,000 | | ✓ | |
| መ | የውሀ ቀለም (Water Based Paint) | ጋሎን | 5- 10 | | ✓ | |
| ሠ | የብረት ቀለም (Enamel Piant) | ጋሎን | 0.5-1 | | ✓ | |
| ረ | ቫርኒሽ (Varnish) | ጋሎን | 0.25-0.5 | | ✓ | |
| ሰ | ማጣበቂያ (Adhesive/Glue) | ጋሎን | 0.25-0.5 | | ✓ | |
| 9.4 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የፕላስቲክና ጎማ ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | የተሽከርካሪ ጎማ (48 የጎማ አይነቶች) | በቁጥር | 6-12 በየጎማው ዓይነት | | ✓ | |
| ለ | የጎማ ኢነር ቲዩቦች (በየ ጎማው ዓይነት) | በቁጥር | 5-8 በየጎማው ዓይነት | | ✓ | |
| ሐ | የፕላስቲክ ፓይፕ (hdpe,pvc,upvc,ppr) | በሜትር | 0.5ሜትር | | ✓ | |
| መ | ፒፒ ከረጢት (pp bag for cement packing, agro sak) | በፒስስ | እስከ 5 በቁጥር | | ✓ | |
| ሠ | ፒኢቲ ፍሊክስ፣ ፒኢቲ ቺፒስ፣ ግራኑል | በኪሎ ግራም | 5-30 በኪሎ ግራም | | ✓ | ኤክስፖርት እየተደረገ ያለ |
| ረ | ስፖንጅና ፍራሽ | በቁጥር | ከየምርት ዓይነቱ 4 በቁጥር | | ✓ | በኤክስፖርት ደረጃ እየተመረተ ያለና ኤክስፖርት ሊደረግ የሚችል |
| ሰ | ፒቪሲ ሲሊንግ | በቁጥር<br>በሜትር (የአንዱ ግራም) | 4 ከየምርቱ ዓይነት<br>0.5ሜትር | | ✓ | በኤክስፖርት ደረጃ እየተመረተ ያለና ኤክስፖርት ሊደረግ የሚችል |
| ሸ | ግሪን ሀውስ ሺት | በኪሎግራም | እስከ 30 ኪሎ ግራም | | ✓ | በኤክስፖርት ደረጃ እየተመረተ ያለና ኤክስፖርት ሊደረግ የሚችል |
| ቀ | ፒቪሲ ኮምፓውንድ | በኪሎግራም | እስከ 100 ኪሎ ግራም | | ✓ | በኤክስፖርት ደረጃ እየተመረተ ያለና ኤክስፖርት ሊደረግ የሚችል |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2



የኢትዮጵያ ... ቤተ መዛግብት
N.
Ethiopian Customs
Records & Docu...

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት አይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| በ | የፕላስቲክ ጫማዎች | በጥንድ | 12ጥንድ በቁጥር | | ✓ | ኤክስፖርት እየተደረገ ያለ |
| ተ | ፒኢቲ ፕሪፎርም፣ ክዳኑ | በቁጥር | በቁጥር ከ500 እስከ 1500 | | ✓ | ኤክስፖርት እየተደረገ ያለ |
| ቸ | የቤት መገልገያ የፕላስቲክ ቁሳቁሶች (ሳህን፣ መጠጫዎች፣ ፊርሙዝ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ጀሪካን፣ ምንጣፍ፣ ኳስ፣ መጥረጊያ ወዘተ) | በቁጥር | ከ6እስከ 10 በቁጥር | | ✓ | በኤክስፖርት ደረጃ እየተመረተ ያለና ኤክስፖርት ሊደረግ የሚችል |
| ኀ | ፍሌክሲብል ፓኬጅንግ (የኤል ዲፒ ሺት፣ ፖሊ ሺት፣ኤል ኤል ዲፒ ሺት፣ ሊብልስ እና ሽሪንክስ፣ ሲፒፒሺት፣ ቢኦፒፒ ...የመሳሰሉት ለማሸጊያ የሚሆኑ የፕላስቲክ ምርቶች) | በኪሎ ግራም | እስከ 50 ኪሎ ግራም | | ✓ | |
| ነ | የፕላስቲክ ገመዶች (ፖሊስተር ገመዶች፣ ስትራፕስ፣ ሞኖ ፊላመንትስ) | በኪሎ ግራም | እስከ 50 ኪሎ ግራም | | ✓ | |
| ኘ | የፕላስቲክ የጌጣ ጌጥ ምርቶች | በኪሎ ግራም | እስከ 0.5 ኪሎ ግራም ያልበለጠ | | ✓ | |
| 9.5 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የፐልፕ፣ ወረቀትና ሕትመት ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | ፐልፕ /Pulp/ | በኪሎ ግራም | ከ250 ኪ፡ግ ያልበለጠ | | ✓ | |
| ለ | ወረቀት /የተለያየ ሳይዝ በሮል ፎርም/ | በኪሎ ግራም | ከ100 ኪ፡ግ ያልበለጠ | | ✓ | |
| ሐ | ካርቶን /ለማሸጊያነት የሚያገለግል በተለያየ ሳይዝ የሆነ ህትመት ቢኖረውም ባይኖረውም/ | በቁጥር | ከ 15 ያልበለጠ | | ✓ | |
| መ | የሴቶች የንፅህና መጠበቂያ /ሞዴስ -Tampons of varying size / | በፓኬት (እሽግ) | ከ 5 ያልበለጠ | | ✓ | 1 ፓኬት (እሽግ) ከ 7 እስከ 12 የሚደርሱ ፒሶች ሊኖሩት ይችላሉ) |
| ሠ | የሕፃናት የንፅህና መጠበቂያ /ዳይፐር -Diapers of varying size / | በፓኬት (እሽግ) | ከ 2 ያልበለጠ | | ✓ | 1 ፓኬት (እሽግ) እስከ 80 የሚደርሱ ፒሶች ሊኖሩት ይችላሉ) |
| ረ | የሕትመት (Printing) ወረቀቶች /የተለያየ A1, A2, A3, A4 እና የተለያየ መጠን ያላቸው/ | በፓኬት (እሽግ) | ከ 2 ያልበለጠ | | ✓ | 1 ፓኬት (እሽግ) እስከ 500 የሚደርሱ ፒሶች ሊኖሩት ይችላሉ) |
| 9.6 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የማዳበሪያና ፔትሮ ኬሚካል ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | የሞተር ዘይቶች | ሊትር | 25 ሊትር | | ✓ | |
| ለ | የጥርሳጥርስ ዘይት | ሊትር | 25 ሊትር | | | |

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2
Ethiopian Customs Records & Documentation No.

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት አይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| ሐ | ግሪስ | ኪ.ግ | 30 ኪ.ግ | | ✓ | |
| መ | የፍሬን ዘይት | ሊትር | 25 ሊትር | | ✓ | |
| ሠ | የሀይድሮሊክ ዘይቶች | ሊትር | 25 ሊትር | | ✓ | |
| ረ | የኢንዱስትሪ ዘይቶች | ሊትር | 25 ሊትር | | ✓ | |
| ሰ | የትራንስፎርመር ዘይቶች | ሊትር | 15 ሊትር | | ✓ | |
| ሸ | የመሪዘይት | ሊትር | 25 ሊትር | | ✓ | |
| 9.7. | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የሲሚንቶና ተዛማጅ ምርቶች ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | ሲሚንቶ (ኦፒሲ እና ፒፒሲ) | ኪሎ ግራም | 100 ኪ.ግ (አንድ ኩንታል) | | ✓ | ለናሙናነት ወደ ውጭ የሚላከው የሲሚንቶ ምርት መጠን 100ኪ.ግ (አንድ ኩንታል) ነው |
| ለ | ክሊንከር (Clinker)(በከፊል ያለቀ ሲሚንቶ) | ኪሎ ግራም | 100 ኪ.ግ (አንድ ኩንታል) | | ✓ | ለናሙናነት ወደ ውጭ የሚላከው የክሊንከር ምርት መጠን 100ኪ.ግ (አንድ ኩንታል) ነው |
| ሐ | ጅፕሰም ፓውደር (ለቻክ እና ለቅርጻ ቅርጽ) | ኪሎ ግራም | 100 ኪ.ግ (አንድ ኩንታል) | | ✓ | ለናሙናነት ወደ ውጭ የሚላከው የጅፕሰም ፓውደር ምርት መጠን 50ኪ.ግ ለቻክ እና 50ኪ.ግ ለቅርጻ ቅርጽ ነው |
| መ | ጅፕሰም ፓርቲሽን ቦርድ Thickness:-1cm Partition board Size 240cm x 120cm | ካሬ ሜትር | 2.88 ካ.ሜ (አንድ ቦርድ) | | ✓ | ለናሙናነትወደውጭየሚላከውየ ጅፕሰም ፓርቲሽን ቦርድ ምርትመጠን 2.88 ካ.ሜ ነው |
| 9.8 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የሴራሚክና ተዛማጅ ምርቶች ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | Wall tiles (varying size & color) | በቁጥር( *pcs)* | *10-24* | | ✓ | |
| ለ | Floor tiles (varying size & color) | በቁጥር( *pcs)* | *10-24* | | ✓ | |
| ሐ | Marble floor tiles (varying size & color) | በቁጥር( *pcs)* | *2-7* | | ✓ | |
| መ | Marble Thread (varying size & color) | በቁጥር( *pcs)* | *3-5* | | ✓ | |
| ሠ | Marble Risers (varying size &color) | በቁጥር( *pcs)* | *3-5* | | ✓ | |
| ረ | Marble window sill (varying size & color) | በቁጥር( *pcs)* | *1-5* | | ✓ | |
| ሰ | Marble door sill (varying size & color) | በቁጥር( *pcs)* | *1-5* | | ✓ | |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

ኢትዮጵያ ጉምሩክ ... ሰነድ ማጣሪያ ...
No
Ethiopian Customs ...
Records & Docum...

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት አይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| ሸ | Marble slab (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 2-3 | | ✓ | |
| ቀ | Granite slabs (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 2-3 | | ✓ | |
| በ | Granite Thread (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 3-5 | | ✓ | |
| ተ | Granite Risers (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 3-5 | | ✓ | |
| ቸ | Granite window sill (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 1-5 | | ✓ | |
| ኀ | Granite door sill (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 1-5 | | ✓ | |
| ነ | Granite floor tiles (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 2-7 | | ✓ | |
| ኘ | Limestone (varying size & color) | በቁጥር( pcs) | 2-7 | | ✓ | |
| 9.9 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የመስታወት ምርቶች ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | ጠርሙዝ /Bottle/ (የተለያየ መጠን ያላቸው ለምሳሌ 200 እስከ 1000 ሚ.ሊ. የሚደርሱ) | በቁጥር | ከ 300 የማይበልጥ | | ✓ | |
| ለ | ከፋይበር የተሰራ የቆሻሻ ማስቀመጫ/ fiber based waste bin/ ( | በቁጥር | ከ 2 የማይበልጥ | | ✓ | |
| ሐ | የውሃ ታንከር(የተለያየ መጠን ያላቸው ከ500 ሊትር ጀምሮ) | በቁጥር | ከ 3 የማይበልጥ | | ✓ | |
| መ | ሻወር ትሪ ከነ ቦክሱ(shower trree) (60*60 ካሬ ሳ.ሚ ጀምሮ) | በቁጥር | ከ 3 የማይበልጥ | | ✓ | |
| ሠ | ሻወር ገንዳ(መዋኛ) (30*120 ካሬ ሳ.ሚ ጀምሮ) | በቁጥር | ከ 3 የማይበልጥ | | ✓ | |
| ረ | ብርሃን አስተላላፊ የጣራ ክዳን፡ ኢጋ ሽት(transparent roof sheet) 30*100 ካሬ ሳ.ሚ ጀምር | | | | ✓ | |
| ሰ | የሽንት ቤት መቀመጫ (10*50 ካሬ ሳ.ሚ ጀምሮ) | በቁጥር | ከ 3 የማይበልጥ | | ✓ | |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

Ethiopian Customs
Records & Docum

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት አይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| 9.10 | ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ከውጭ የሚገቡ የእንጨትና ተዛማጅ ምርቶች ምርት ናሙናዎች መጠን | | | | | |
| ሀ | ፕላይ ውድ<br>(Plywood)<br><br>Sheet sizes: 2400mm x 1200mm<br><br>Sheet Thickness: 4, 6, 9, 12, 15, 17, 25, 27, 33mm | ሜትር ኪዩብ | 0.095$m^3$ | | ✓ | የተቀመጠ የናሙና ምርት የመጠን መለኪያ ለአንድ ፕላይ ውድ ምርት ሲሆን ምርቱን የሚልከው አምራች ድርጅት በአንድ ምርት መጠን 0.095$m^3$ በላይ መሆን የለበትም |
| ለ | ቬኔር<br>(Veneer)<br><br>Thickness of 0.6 mm to 4.8 mm<br><br>Maximum Sheet Size 80mm x 1000mm<br><br>Minimum Sheet Size200mm x 3000mm | ሜትር ኪዩብ | 0.003 $m^3$ | | ✓ | የተቀመጠ የናሙና ምርት የመጠን መለኪያ ለአንድ ቬኔር ምርት ሲሆን ምርቱን የሚልከው አምራች ድርጅት በአንድ ምርት መጠን 0.003 $m^3$በላይ መሆን የለበትም |
| ሐ | ኤምዲኤፍ<br>MDF (Medium density Fiber)<br><br>Available Thicknesses; 3mm,4mm, 6mm, 9mm, 12mm, 15mm, 18mm, 22mm, 25mm<br><br>Maximum Sheet Size 2420mm x 1220mm<br><br>Minimum Sheet Size100mm x 50mm | ሜትር ኪዩብ | 0.073$m^3$ | | ✓ | የተቀመጠ የናሙና ምርት የመጠን መለኪያ ለአንድ ኤምዲኤፍ ምርት ሲሆን ምርቱን የሚልከው አምራች ድርጅት በአንድ ምርት መጠን 0.073$m^3$ በላይ መሆን የለበትም |
| መ | ኤችዲ ኤፍ<br>HDF (High Density Fiber)<br><br>Available Thicknesses; 3mm,4mm. 6mm, 9mm, 12mm, 15mm, 18mm, 22mm, 25mm<br><br>Maximum Sheet Size 2420mm x 1220mm<br><br>Minimum Sheet Size100mm x 50mm | ሜትር ኪዩብ | 0.073 $m^3$ | | ✓ | የተቀመጠ የናሙና ምርት የመጠን መለኪያ ለአንድ ኤችዲ ኤፍ ምርት ሲሆን ምርቱን የሚልከው አምራች ድርጅት በአንድ ምርት መጠን 0.073 $m^3$ በላይ መሆን የለበትም |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2



Ethiopian Customs
Records & Docu

| ተ.ቁ | በኤክስፖርት ፖቴንሻል የተያዙ የምርት አይነት ስም | ለኤክስፖርት (ወጪ ንግድ) የሚላክ ናሙና | | ለናሙና የሚላከው ምርት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | ምርት መጠን (ብዛት) | ተመላሽ የሚደረግ | ተመላሽ የማይደረግ (የማይመለስ) | |
| ፲፱ | ችፕ ውድ<br>Particle board<br><br>Thickness:- 9mm, 11mm, 12mm, 17mm, 18mm, & 25mm<br><br>Maximum Sheet Size 2743.2 x1828.8<br><br>Minimum Sheet 1828.8 x 914.4 | ሜትር ኪዩብ | 0.125$M^3$ | | ✓ | የተቀመጠ የናሙና ምርት የመጠን መለኪያ ለአንድ ችፕ ውድ (Particle board) ምርት ሲሆን ምርቱን የሚልከው አምራች ድርጅት በአንድ ምርት መጠን 0.125$M^3$ በላይ መሆን የለበትም። |
| ፳ | ባምቡ ፍሎሪንግ<br>Bamboo Flooring<br><br>• Solid Bamboo Plank sizes: 13 mm, 11 mm, and 16 mm (5/8')<br><br>thick x 75 mm (3"), 95 mm (3-3/4"), 190 mm (7 1/2"), 300 mm (12")<br>wide x 600 mm (24"), 915 mm (36"), and 1830 mm (72") long.<br><br>• Engineered Bamboo Plank Flooring sizes: 16 mm (5/8")<br>Thick x 137 mm (5-3/8") and 190 mm (7 1/2")<br>wide x 1830 mm (72") long.<br><br>• Strand Bamboo Plank sizes: 10 mm (3/8") and 16 mm (5/8")<br>thick x 95 mm (3-3/4") and 190 mm (7 1/2")<br>wide x 915 mm (36") and 1830 mm (72") long.<br><br>• Solid / Engineered / Strand Bamboo Tile sizes: 13 mm (1/2"), 11 mm (7/16"), and 16 mm (5/8')<br>Thick (depending on type) x 305 mm (12") square and 305 mm x 610 mm (12" x 24"). | ሜትር ኪዩብ | 0.009$M^3$ | | ✓ | የተቀመጠ የናሙና ምርት የመጠን መለኪያ ለአንድ ባምቡ ፍሎሪንግ ( Bamboo Flooring) ምርት ሲሆን ምርቱን የሚልከው አምራች ድርጅት በአንድ ምርት መጠን 0.009$M^3$በላይ መሆን ያለበትም |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2



Ethiopian Customs
Records & Documen
No.

9.11 በዚህ አንቀጽ አምራች ላኪዎች ለገዥዎች ምርቱ የተሰራበትን ግብዓት ናሙና የሚልኩ ከሆነ ሁሉም ናሙናዎች ከ1ኪ.ግ ያልበለጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም አሠራር ይህንን በዚህ መመሪያ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

11. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

12. መመሪያን ስለ ማሻሻል

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በባህሪው በየጊዜው ተለዋዋጭ በመሆኑ ምክንያት ለወጪ ንግድ የሚመረቱ ምርቶችም ሆኑ ምርቶቹን ለማምረት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ግብዓቶች በቁጥርም ሆነ በዓይነት በየጊዜው ሊለዋወጡ የሚችሉ በመሆኑ ይሄው ታይቶ ሚኒስቴሩ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚቀርብለት ሀሳብ መሠረት ይህን መመሪያ ሊሻሻል ይችላል፡፡

13. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ________________ ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 01 ቀን 2014 ዓ.ም.

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር